***Journal of Afroasiatic Languages/Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL)***

Volume 14, Number 1, 2025

# የትውስታዎቼ መጽሐፍ ዳሰሳ

ዳንኤል ካሳሁን

**ዓለምአንተ ገብረሥላሴ (2024 እኤአ)። ትውስታዎቼ: *ስለመሬት ይዞታና የተለያዩ ፖለቲካዊና አገራዊ ገፅታዎች።* ትሪንተን፤ ዘ ሬድ ሲ ፕሬስ፣ ገፅ ብዛት 267።**

ዓለምአንተ ገብረሥላሴ የልጅነትና የዩኒቨርሲቲ ትውስታውን፣ የመሬት ይዞታ ጥናትና እና የመሬት ላራሹ አዋጅ ተሳትፎውን፣ በትግራይና በበጌምድር የነበረውን የትጥቅ ትግሉን፣ በሱዳን እና በፈረንሳይ ያሳለፈውን የስደት ዘመኑን፣ በአሜሪካ የኖረበትን አካዳሚያዊና ፖለቲካዊ ሕይወቱን፣ ወዘተ በ"ትውስታዎቼ" መጽሐፉ አካቷል። ሆኖም በጥልቀትና በስፋት የተዳሰሰው ጉዳይ የመሬት ይዞታ ጥናትና እና የመሬት ላራሹ አዋጅ ተሳትፎውን በመሆኑ የዚህ የመጽሐፍ ዳሰሳ በመሬት ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።

የዓለምአንተ ትውስታዎቼ ከተለመዱ ግለ ታሪኮች ለየት ይላል። በሥር ነቀሉ የገጠር መሬት አዋጅ መረቀቅና መተግበር ላይ የነበረውን የግል እና የቡድን ተሳትፎውን ተመርኩዞ፤ በአዋጁ ዙሪያ ሲቀርቡ ከቆዩ የተሳሳቱ ትችቶችና ትርክቶች መክቷል። አከራካሪ ሆነው የቆዩ ጉዳዮችን ደግሞ በጊዜ ሂደት ነጥረው በወጡ ፖለቲካዊ እና የኢኮኖሚያዊ ዕይታዎች አንፃር ቃኝቶ ለአንባቢ አቅርቧል። ስለሆነም መጽሐፉ እንደሚከተለው ጠለቅ እና ሰፋ ያለ ዳሰሳን ጋብዟል።

## 1. የመሬት ይዞታ ጥናት እና የአዋጁ ትውስታ

"*የአዋጆች ሁሉ እናት*" (ቤሉቺ, 2016)፣ "*የአከራሪ የግራ ተቃዋሚዎችን እንኳ ያስገረመ*" (ባህሩ፣ 1999) ወዘተ ለተሰኘው ሥር ነቀሉ የ1967 ዓ.ም የመሬት ላራሹ አዋጅ ዓለምአንተ ዕድሜ ልኩን ሲዘጋጅበት የቆየበት የሚመስል ነው። የድካሙን ፍሬ በለጋ ዕድሜው[1] ለማየት በቅቶ ከግማሽ ምዕተዓመት በኋላ ትውስታውን ለአንባቢ ማካፈሉ ዕድለኛነቱን ይመሰክራል። ዓለምአንተ እንደሚነግረን አባቱ በተለያዩ ወረዳዎችና አውራጃዎች ለሥራ ሲዘዋወሩ ከተገነዘቡት ጉዳዮች መሀል በበጌምድር ገበሬ ጫንቃ ላይ እስከ 26 የግብር

1 ዓለምአንተ የተወለደበትን በማስላት የመሬት አዋጁ በ29 ዓመቱ፣ የከተማ ትርፍ ቤት አዋጁ በ30ኛ ልደቱ ሐምሌ 19 ነበር።

ዓይነቶች ቀንበር እንደተጫነበት ነግረውት ሰቆቃው በጨቅላ አዕምሮው ተቀርጿል። ከቀኃሥ ዩኒቨርሲቲ በሕግ ከተመረቀ በኋላ የአገልግሎት ግዳጁን በመሬት ስሪት ሚኒስቴር ተመድቦ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት ቁኒ ወረዳ የሥራ ልምድን አካብቷል። በዴሳ ቀበሌ ላይ በአንድ የሰባ ዓመት አዛውንት ላይ ደርሶ የነበረ አስከፊ ሰቆቃን ተመልክቶ ጎንደር ሳለ ከሰማው ችግር በላይ ልቆበት ልቡ ተነክቷል። ቀድሞ ተማሪ ሳለ በጓደኞቹ ጉትጎታ ፖለቲካዊ ንቃቱን እንዲያዳብር የተሰጠውን ምክር ከቁብ ያልቆጠረው ዓለምአንተ የበዴሳው አጋጣሚ ዐይን ገላጭ ሆኖለት የግራ ዘመም መፃሕፍትን በትኩረት እንዲያነብ ተቆስቁሷል። በቀጣይም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን በሕግ አማካሪነት ተቀላቅሎ የመሬት ስሪቱን ለማጥናት ከባሌና ከወለጋ በቀር በመላው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛቶች ተዘዋውሯል። ስኮላርሺፕ አግኝቶ ለሁለት ዓመታት አሜሪካን አገር በዩስኮንሲን ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት በመሬት ጥናት ሰልጥኗል፣ ወዘተ። ይህን ሁሉ ዘርፈ ብዙ የሕይወት፣ የትምህርት፣ እና የሥራ ልምድ ዝግጅቶችን አዋህዶ ዓለምአንተ ከሥር ነቀሉ የየካቲት 1967 የመሬት አዋጅ አርክቴክቶች መሀል ቀዳሚው ቢባል አይበዛበትም።

በትውስታዎቼ ላይ ዓለምአንተ በበርካታ ጠቅላይ ግዛቶች በመስክ ተገኝቶ አንኳር የሚባሉ የመሬት ስሪቶችን በመተንተን በኢትዮጵያ ያሉ የመሬት ስሪቶች ከስፍራ ስፍራ የሚመሳሰሉበት ጠባይ አሳይቷል፤ ፍጹም የሚለያዩበት ጠባያት እንደነበሩትም አስገንዝቧል። መጽሐፉ በወቅቱ የነበረውን የመሬት ጉዳይና የፖለቲካ ድባብ ለመረዳት የሚያገለግል ብቻ አይደለም። በቀጣይ ዓመታት በገበሬው ህይወት ላይ የተስተዋሉ አሉታዊና አዎንታዊ አንድምታዎችንም መመርመር ለሚሹ አጥኚዎችም የመረጃ ቋት (*treasure-trove of information እንዲሉ*) ነው። ደራሲው ኢህአፓን ተቀላቅሎ ደርግን ለመፋለም ሲነሳ ይዞት የቆየውን የቋሚ ተጠሪነት ሥልጣን እርግፍ አድርጎ፣ ከተራ ታጋይነት[2] እስከ ኮሚሳርነት ተሰልፎ በአሲምባ፣ በጠለምት፣ በጭልጋ፣ በሰሜን ተራራ፣ ወዘተ የተካሄደ ፈታኝ የትጥቅ ትግልና የስደት ሕይወትን አልፎ፣ ሃምሳ ከሚጠጉ ዓመታት በኋላ በጊዜ ርዝማኔ ባልወየበ ሁኔታ የቦታ ስም፣ የሰዎች ስም፣ የዘመን መረጃን አስታውሶ ይህን በመረጃ የዳበረና ፍሰቱ የማይጎረብጥ መጽሐፍ ማበርከቱ የሚደነቅ ነው፤ ሊመሰገንም ይገባዋል።

ከመፅሐፉ መረዳት የሚቻለው በረቂቅ አዋጁ ዝግጅት ሂደት በርካታ ሥጋቶች ተሸንቅረውበታል፣ የተለያዩ ዕሳቤዎችና አማራጭ ሃሳቦች ተስተናግደውበታል። አዋጁ በርካታ ባለድርሻ አካላት የነበሩትና ተዋናዮችም "ተራማጅ" ተብለው በጥቅል ይጠሩ እንጂ በዓላማ፣ በፖለቲካ ቀለም፣ በአካዳሚያዊ ዝግጅታቸውና በወከሉት ማኅበረሰብ ወይንም ድርጅት አይነቶች የተዥጎረጎረ ነበር። ረቂቁን ካዘጋጁት ከአስሩ የመሬት ይዞታ ሚኒስቴር "ተራማጅ" ምሁራን ባሻገር የጭላሎ እርሻ ልማት (ካዱ) ኤክስፐርቶች፣ ፖለቲከኞች፣ የደርጉ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኮሚቴ አባላት፣ ወዘተ ግራ-ዘመም የሆነ ሥር ነቀል አዋጅ

2 ዓለምአንተ ከነበረው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ እና የሥልጣን እርከን አንፃር ራሱን "ተራ ታጋይ " ብሎ በመጽሐፉ መግለፁ ትህትናውን ያሳያል።

እንዲታወጅ ከፍተኛ ጫና ማሳረፋቸው ተስተውሏል። በተጨማሪ የስዊድን እና የአሜሪካ መንግሥታት እና በርካታ የደርጉ አባላት[3] ለዘብ ያለ የመሬት ማሻሻያ አዋጅ እንዲታወጅ ሲጥሩ ነበር[4]። በሌላ በኩል የሶቭየት፣ ዩጎዝላቪያ፣ እና የቻይና ኤምባሲ ባለሥልጣናት የተረቀቀው ሥር ነቀል መሬት አዋጅ ቢታወጅ ሊያስከትል የሚችለውን የኢኮኖሚና ማኅበረሰባዊ ምስቅልቅል በመስጋት አዋጁ በፍጥነት እንዳይተገበር ሻለቃ መንግሥቱን በይፋ ተማጽነዋል። "*አገራችን ባደረግነው ሥር ነቀል የመሬት አዋጅ ሳቢያ ተከትሎ ከመጡብን ችግሮች ተማሩ*" (ኮኸን, 1987) ብለው በመምከራቸው ሻለቃ መንግሥቱ የመወላወል ዝንባሌ አሳይተው እንደነበርና (ገፅ 98) ይህ ደግሞ በሻምበል ሞገስ ወልደሚካኤል ላይ ስጋት ፈጥሮ እንደነበር ተስተውሏል። በመጽሐፉም ሆነ በሌሎች በቀጥታና በግልፅ አይነገር እንጂ የመሬት አዋጁ ወደ ግራ በመዘመም ስር ነቀል እንዲሆን የአንበሳውን ድርሻ የወሰደው የደርጉ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኮሚቴ ሊቀ መንበር ሻምበል ሞገስ እንደነበረ መገመት ይቻላል[5]።

በመፅሐፉ የመሬት ይዞታ መጠን ጣራውም በዋልታ–ረገጥ አማራጮች የተወጠረ ነበር። ባንዱ ጠርዝ እስከ አሥር ጋሻ ይሁን የሚል ሐሳብ በዶክተር ክፍሌ ገብሩ ሲቀርብ በሌላ ጠርዝ ደግሞ እነ አቶ ታየ ጉርሙ እና ሻምበል ሞገስ መሬቱ የመንግሥት እንዲሆን መሻታቸው የሂደቱን ፈተና የሚያሳይ ነው። ውጥረቶቹን እና ጫናዎችን አቻችሎ አዋጁ የብዙሃኑን ስምምነት አግኝቶ 26 ሚሊዮን ሕዝብን ለያዘች አገር እንዲያገለግል መጽደቁና መተግበሩ ዓለምአንተን ጨምሮ በርካታ የሕግ ባለሞያዎች፣ የደርግ መኮንኖች፣ ዘማቾች፣ ወዘተ ከፍተኛ መስዋዕትነት ስለከፈሉበት መሆኑን ከመጽሐፉ ለመረዳት ይቻላል። በመጨረሻ መሬት የማይሸጥ፣ የማይለወጥ፣ በወለድ አገድ የማይያዝ፣ በኪራይ መልክ ወደሌላ የማይተላለፍ ሆኖ ተደነገገ። በወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ የአዋጁ አንቀጾች የራሳቸው ጠቀሜታ እንደነበራቸው በመጽሐፉ ቢሞገትም ጉዳዩ ዘርፈ ብዙ አንድምታዎችን አስከትሏልና እስከዛሬ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ ቀይቷል፤ ተከታታይ አካዳሚያዊ ወይይትንም ይጋብዛል።

---

3 ጥቂት የማይባሉ የደርጉ አባላት በንጉሠ ነገሥቱ የመሬት ዳረጎት የተደርገላቸው የመሬት ባለንብረቶች ነበሩ።

4 ምዕራባውያኑ በኢትዮጵያ ለዘብተኛ አዋጅ ወጥቶ የገበሬው ሕይወት በመጠኑ እንዲሻሻል እንጂ የከረረ ሥር ነቀል አዋጅ ወጥቶ ለኮሚኒስት አገራት በሩን እንዳይከፍት ይሹ ነበር (ገፅ 81)። በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ኮሚኒዝም እንደ ሰደድ እሳት (በዶሚኖ ኢፌክት) በበርካታ የኢስያ፣ አፍሪካ፣ እና ላቲን አሜሪካ እየተስፋፋ ስለነበር (ጋዲስ, 2005) ኢትዮጵያም በዚህ ወረራ እንዳትጠለፍና ከኮሚኒስት ጎራ እንዳትሰለፍ ይሰጉ እንደነበር ተገልጧል።

5 ሻምበል ሞገስ ለዓለምአንተ ስለ ከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጅ አስፈላጊነት ሽንጡን ገትሮ ሲሚገት "*In principle አከራይና ተከራይ የሚባል ነገር መኖር የለበትም*" (ገፅ 124) ሲል በአፅንኦት መናገሩ የግራ አክራሪ ፖለቲከኛነቱን ይመሰክራል።

## 2. የመሬት አዋጁ ትሩፋት

የመሬት አዋጁ የባላባታዊ ሥርዓቱ መገለጫ የሆነባቸውን የተወሳሰበ፣ የተንዛዛ እና አሰቃቂ የመሬት ስሪት ከሥሩ መንግሎ መጣሉ ትልቁ ስኬት እንደሆነ ዓለምአንተ መግለፁ ከሌሎች በርካታ ጸሐፊዎችና ፖለቲከኞች ያስማማዋል። በሥር ነቀል የመሬት አዋጅ ሳቢያ እነ ሶቪየት ሕብረት አያሌ ቁጥር ላለው ሕዝብና ለከብቶች ውድመት ተጋልጠው ሳለ በኢትዮጵያ ግን ተመሳሳይ ቀውስ ቢያንስ ወዲያውኑ አለመከሰቱ ሌላው የአዋጁ ስኬት መባሉም አያከራክርም።

ሌላው የተጠቀሰው ትሩፋት "*ከአዋጁ በኋላ አርሶአደሩ የጉልበቱን ፍሬ ማንም ሳይካፈለው ለራሱና ለቤተሰቡ ፍጆታ ብቻ ማድረጉ*" (ገፅ 120) የተባለው ነው። እርግጥ የቀድሞው ባላባት ከአዋጁ በኋላ የገበሬውን ምርት አይካፈለውም። ነገር ግን መንግሥት በሂደት ባላባቱን ተክቶ የገበሬውን ምርት ሲካፈል እንደነበረ በገሃድ የታየ ነው። አርሶ አደሩ ምርቱን መንግሥት በደነገገው ዝቅተኛ ዋጋ ለመንግሥት ብቻ እንዲያቀብ ተብሎ የተቋቋመው የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት እንዲሸጥ ይገደድ ስለነበር (ባሕሩ, 1999፡ 254) እና አርሶ አደሩ ያመረተው ምርት በአይነትና በመጠን የተጣለበትን ኮታ ማሟላት ስለማይችል ከብቶቹን ሸጦ ከገበያ በውድ ዋጋ ገዝቶ በኪሳራ ለኮታ ማሟያ የሚያስረክብባቸው አጋጣሚዎች ነበሩና ደራሲው አባባሉን መጥኖ ሊያቀርበው የሚገባ ጉዳይ ነው።

በቀጣይ የተነሳው ስኬት በመሬት ክርክር ሳቢያ በየፍርድ ቤቶችና በአስተዳደር አካሎች ይጠፋ የነበረው ጊዜ ፈፅሞ ተወግዶ ለገበሬው ትልቅ እፎይታ መስጠቱ ነው። ይህ አባባል ከፍተኛ የደርጉ ባለሥጣናት በፃፏቸው መፃህፍትም የተስተጋባ ቢሆንም ስኬቱ ቅቡል የሚሆነው የመሬት አዋጁ እስኪታወጅ የነበረውን ለዘመናት እየተንከባለለ እልባት ሳያገኝ የቆየ የመሬት ክርክሮችን በተመለከተ ከሆነ ነው። እርግጥ ነው የመሬት አዋጁ ይህን ሆሉ በአንድ ቀን ሽሮታል።

ከአዋጁ በኋላ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችንና ክርክሮችን በተመለከተ ግን ገበሬው ያገኘው እፎይታ አከራካሪ ነው። በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን የነበረው የፍርድ ሥርዓት ተበዳዩ ገበሬ ዝቅተኛ እርከን ላይ ባለ ፍርድ ቤት ውሳኔ ካልረካ ደረጃው ከፍ ወዳለ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ እያቀረበ እስከ አዲስ አበባ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ አቤቱታ የማሰማት ዕድል ነበረው። እርግጥ ነው የአቤቱታ ብዛትና የፍርድ ቤቶች ብዛት ባለመጣጣማቸው እንዲሁም ሥርዓቱ ለባላባቶች የሚያደላ በመሆኑ ብዙ ግፍና መጉላላት ነበረ። ነገር ግን የጭላንጭል ታህልም ብትሆን ተስፋ ስለነበረው "*ይፈረድልኛል*" ብሎ ሙከራ ያደርግ ነበር። ከመሬት አዋጁ በኋላ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሰፈነው የመሬት ነክ ፍርድ ይግባኝ የሌለውና ብያኔ የሚሰጠው ደግሞ የሕግ መሠረታዊ እውቅትና ልምድ በሌላቸው የገበሬ ማኅበራት ተመራጮች ሆኖ ነበር። ይህ አሰራር ለተቃውሞና ቅሬታ መፈናፈኛ ስለሌለው የፈለገው ነገር ገበሬው ላይ ቢወሰን "*አሜን*" ብሎ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረውም። ስለዚህ ከመሬት አዋጁ በኋላ የሰፈነው የመሬት ፍርድ ሂደት የራሱ አስከፊ ገፅታ እንደነበረው ሊዘነጋ አይገባም። እንደውም ከደራሲው ድምዳሜ ፍፁም የተቃረኑ

አይታዎችም እንደነበሩ ለመገንዘብ አበራ የማነ አብ (2016) የተናገረውን "*መሬት ላራሹ የመጣው ኪሳራን ነበር*" መጥቀስ ይቻላል።

## 3. የተሳሳተ ትርክትን ማቃናት

የተሳሳተ ትርክትን በማስተካከል ረገድ ከመጽሐፉ ሶስት ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) መሪዎች ለትጥቅ ትግል አነሳስቶናል ብለው ያቀረቡትን የተሳሳተ ምክንያት ነው። "*ማዕከላዊ መንግሥት በልማት መስክ ትግራይን ሆን ብሎ እንዳገለለና ለአማራው ሕዝብ ያደርግ የነበረው አድሎ ብለው ያሉት ሐሰተኛ ትርክት ተከታዮቻቸውን ብቻ ሳይሆን የውጭ አገር መንግሥታትንም ለመሳመን ሞክረዋል*" (ገፅ 13)። ዓለምአንተ ይህን የተሳሳተ ትርክት የሞገተው በመስክ ጉብኝቶቹ ወቅት የታዘበውን ተመርኩዞ፣ ትግራይን ከጎንደር ጠቅላይ ግዛት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ አቅርቦት ጋር በማመሳከር ነው። የትግራይ አብዛኞቹ ወረዳዎች እርስ በርስ በመኪና መንገድ ተገናኝተው ነበር። የጠቅላይ ግዛቱ ገዢ ልዑል ራስ መንገሻ ከሌሎች አቻ ገዢዎች በተለየ መልኩ ከውጭ አገር መንግሥታት ጋር በቀጥታ ስለ ልማት ለመነጋገርና ለመተባበር ዕድል እንደነበራቸውና ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ፣ መንገድ[6]፣ የልማት ተቋማትን ያስፋፉ እንደነበር አድንቆ በተቃራኒው የጎንደሩ ገዢ ደግሞ ኋላ ቀር አስተሳሰብ የተጠናወታቸውና በገበሬዎች መዋጮ ተቀጥሮ የነበረ የቄስ አስተማሪን እንኳ በአሽከራቸው በማስደብደብ ከቀዬው አባርረው እንደነበር የታዘበውን አጋርቷል። በወቅቱ የጎንደሩ ገዢ ሶስት ዓበይት የሥራ ድርሻ ነበረው፤ ግብር ከመሰብሰብ፣ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ከማስመረቅ፣ እና ፀጥታን ማስከበር ባሻገር የልማት ጉዳይን እንደማይከታተል ተገንዝቧል። ትግራይን በፅኑ የጎዳው የተደጋጋሚ ድርቅ ችግርና መንግሥት ለችግሩ ፈጥኖ ያለመድረስ ድክመት ቢሆንም ይህ ክስተት ደግሞ በወሎም ቢሆን በተባባሰ መልኩ ተከስቶ የነበረ ጉዳይ እንደነበር ነው።

ደራሲው በሻዕቢያም በኩል በኢትዮጵያና ኤርትራ ሕዝቦች መሀል አንዳችም ታሪካዊ ግንኙነት አልነበረም ተብሎ የሚጠነጠነውን ትርክት ሞግቷል። በመስክ ጉብኝቱ ጎንደር ውስጥ በጭንፍራ ምክትል ወረዳ ያሉ ገበሬዎች ጥንት ከኤርትራ የመጡ ሕዝቦች ነን ብለው እንደነገሩትና አስመራ አካባቢ ለሚገኘው የደብረ-ቢዘን ገዳም ስንዴ እንደሚገብሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኤርትራ ውስጥ በሐማሴን አካባቢ ዓድ ተክለሃን ወረዳ ያሉ ነዋሪዎች በአፄ ሰርፀ ድንግል ዘመን ቱርኮችን ለመከላከል ወደ ኤርትራ ከዘለቀው ጦር ጋር ከደንቢያና ቋራ እንደመጡ የሚናገሩ፣ ከረን ላይ ሀልሀል አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮች ከሮሀ ላሊበላ እንደመጡ፣ ቋንቋቸውም አገውኛ እንደነበር መስክሯል (ገፅ 137)።

ሶስተኛው የተሳሳተ ትርክት ደግሞ የመሬት አዋጁን በማርቀቅ ሂደት ስለተሳተፉ አባላት ነው። አንዳርጋቸው አሰግድን፣ ክፍሉ ታደሰን፣ እና ሻምበል ፍቅረሥላሴን ጠቅሶ በመጽሐፎቻቸው ላይ በመሬት አዋጁ ማርቀቅ ሂደት ጭራሽ ያልተሳተፉ ግለሰቦችን

---

6 ልዑል ራስ መንገሻ ራሳቸው ግሬደር እየነዱ በትግራይ የልማት እንቅስቃሴ በግምባር ቀደምትነት ይሳተፉ እንደነበር ተገልጿል።

ደባልቀው ጠቅሰዋል መባሉ ነው። ዓለምአንተ ዝርዝር መረጃዎችን በማካተት በጉዳዩ ላይ ብዥታ በማጥራቱ በተወሰነ መልኩ በመሬት ላራሹ ታሪካዊ አዋጅ ድርሻ ላይ የታሪክ ሽሚያ እንዳለ ያመላክታል።

## 4. ትችትን መሞገት

ዓለምአንተ በመሬት አዋጁ ላይ ያላግባብ የቀረቡ ትችቶች ናቸው ብሎ ካመነባቸውና ለመሞገት ከጣረባቸው ጉዳያት መሀል መሬት ማከራየት በመከልከሉ፣ መሬት በመንግሥት ሙሉ ቁጥጥር በመዋሉ፣ መሬት መሸጥ መለወጥ በመከልከሉ ላይ የተነሱ ትችቶች ይገኙበታል።

በበርካታ አጥኚዎች[7] በአዋጁ መሬት ማከራየት እና መሸጥ መለወጥ መከልከሉ በሂደት መሬቱ በመንግሥት ሙሉ ቁጥጥር እንዲውል አድርጎ ገበሬው ከባላባት ጭሰኛነት ወደ መንግሥት ጭሰኛነት እንዳሸጋገረው ያመላክታሉ። እኒህን ችግሮች ዓለምአንተ ሙሉ ለሙሉ የተቀበላቸው አይመስልም። "*ማከራየት ቢፈቀድ ባለሃብቶችና ባለርስቶች ጭሰኛው ያገኘውን መሬት በተለያየ መንገድ (በመደለል፣ በአበልጅነት፣ በገንዘብና በማሳሰሉት) መሬቱን እንደገና ይነጥቁታል*" (ገፅ 93) ሲል መሬት ማከራየቱን አስፈላጊነት ይቃወማል። በወቅቱ ከከበው የፖለቲካ አየር ሳቢያ ስጋቱ ቅቡል ቢሆንም ዛሬ ላይ ሆኖ ወደ ኋላ ሲመለከተው ሌሎች የህግ አማራጮች ይኖሩ እንደነበር መገመት አያዳግተም። ደራሲው "*ተቿዎች አዋጁ የገጠር መሬትን የህዝብ ሳይሆን የመንግስት አደረገ የሚሉት አባባል ትክክል ኣይደለም*" (ገፅ 119) ለማለት የሰጠው ምክንያት የአዋጁ እሳቤ እንደዚያ እንዳልነበረ በመግለፅ ነው። ሆኖም መሬት ላይ ያለውና የገበሬውን ህይወት በቀጥታ የተቆጣጠረው የአዋጁ እሳቤ ሳይሆን በግብር የታየው ነገር በመሆኑ ክርክሩም ማተኮር የሚገባው ከተጨባጩ እውነታ በመነሳት መሆን ይኖርበታል የሚል መከራከሪያ ያስነሳል።

ዓለምአንተ መሬት መሸጥ መለወጥን በተመለከተ ትችቶቹ "*የኢትዮጵያ (ኤርትራን ጨምሮ) የመሬት ስሪትን ያላገናዘበ ነው*" (ገፅ 104) ብሎ ከመሞገቱ ባሻገር ቀድሞውኑ በኢትዮጵያ መሬት መሸጥና መለወጥ ባህል አልነበረም ማለቱ የደቡቡን የመሬት ግዢና ሽያጭ ባህል ጉዳይስ ለምን ተዘነጋ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው። ስለሆነም ሙግቱ ተሻሽሎ ሊቀርብ የሚገባው ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ በሰሜን እና ደቡብ ኢትዮጵያ የአገሪቱ ክፍሎች በገበሬው ላይ ይደርስ የነበረው ጭቆና ተመሳሳይነት ነበረው (ገፅ 59) ብሎ ያቀረበው ሐሳብ፣ ቀደም ብሎ ደራሲው ወደ ሐረርጌ ቁኒ በሄደበት ወቅት የበርጫ ክፍያ ሥርዓትን ተመልክቶ በሰሜን ጠቅላይ ግዛቶች ከነበረው የመሬት ስሪት ሲነጻጸር የደቡቡ አስከፊ ሆኖ በማግኘቱ ልቡ ከመነካቱ ሐሳብ (ገፅ 35) ጋር ቢጣጣም መልካም ነው።

ባለፉት አምስት አስርት ዓመታት የተለያዩ አጥኚዎች በመረጃ ላይ እየተመረኮዙ ያጠኗቸው በርካታ ጥናቶች አሉ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ማህበር በተካሄደው

7 ለምሳሌ ደሳለኝ (2011)፣ ባሕሩ (1999)፣ አበራ (2016)፣ ወዘተን መጥቀስ ይቻላል።

ጥናት (ነጋ እና ሌሎች፡ 2003) ገበሬው መሬቱ የግሉ ቢሆን መንግሥት እንደሚለው በቀላሉ እንደማይሸጠው የመሰከሩት ጉዳይ የነበረና በተለይም ማከራየት አለመፈቀዱ እንደ ባላባት ሥርዓት ሁሉ ገበሬውን ለበርካታ ድህነት የዳረገ ጉዳይ መሆኑ ተዘግቧል።

## 5. ስፍራዊ ጠባይ

በንጉሡ ነገሥቱ ዘመን የገበሬው የእርሻ መሬት ይዞታዎች በሶስት ጂኦግራፊያዊ ክፍሎች[8]፤ የሰሜን (ርስት)፣ የደቡብ (የገባር)፣ እና አገሪቱን ዙሪያዋን የከበበው የዘላን (የመንግሥት) ስሪቶች ነበሩ። የርስት እና የገባር ስሪቶቹ አራሽ ገበሬውን ያማከሉ ሲሆን በመሀላቸው በግልፅ የሚታይ የግብር፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የመሬት ለምነት፣ የመሬት ጥበትና ስፋት፣ የገበሬው መሬት ባለመብትነት፣ ወዘተ ልዩነት እንደነበራቸው በ"ትዝታዎቹ"ም ሆነ በሌሎች የተመሰከረ ነው። በዘመናዊ እርሻ መስፋፋት ሳቢያ በገበሬው ደርሶ የነበረው መፈናቀል እጅግ በርክቶ የታየው በደቡቡ የኢትዮጵያ ክፍል ነበር። በንጉሡ ዘመን ሚኒስትሩ አቶ አባይ በለጠ እና ዓለምአንተ የባላባትና የጪሰኛውን ግንኙነት ለማሻሻል የተረቀቀውን አዋጅ ለማስፀደቅ እንዲረዳ የፓርላማ አባላትን ቀድመው ለማግባባት *(ሎቢ ለማድረግ)* ሲሞክሩ ዒላማ ያደረጉት ሰሜን ጠቅላይ ግዛቶችን ከወከሉት የፓርላማ አባላትን እንጂ ደቡብ ወደሚገኙትና ከፍተኛ የመሬት ባለይዞታ ወደነበሩት የፓርላማ አባላትን አልነበረም።

ከላይ የተጠቀሱት የመሬት፣ የገበሬው፣ እንዲሁም የፖለቲካው ከባቢ ሁኔታ ስፍራዊ ጠባይ እንደነበራቸው የሚያሳይ ነው። ታዲያ ሥር ነቀሉ የየካቲት 1967 የመሬት አዋጅ አንድ ወጥ የመሬት ስሪት ለመላው አራሽ ገበሬ እንዲተገበር መታወጁ "የአዋጁ ረቂቅም ሆነ አተገባበር ስፍራዊ ትኩረት የተነፈገው" (ጂኦግራፊካል ነግሊጀንስ[9]) ነበር ለማለት ያስደፍራል። መስፍን ወልደማርያም (2012) የመሬት አዋጁን ከኮነነባቸው ምክንያቶች አንዱ በሰሜን እና በደቡብ ያለውን የመሬት ይዞታ ችግር ተመሳሳይ አድርጎ በመውሰዱ ነበር።

ግራ የሚያጋባው ጉዳይ የመሬት አዋጁን በሰሜን እና ደቡብ ለይቶ የማውጣቱን ጠቀሜታ ለአዋጁ አርቃቂዎች እንግዳ አለመሆኑ ነው። ሁለት ማሳያዎችን እናንሳ። አንደኛው ኮሎኔል ብርሃኑ ባየህ (2013) ያነሳው ትውስታ ነው። ሚኒስትሩ ዘገዬ አስፋውና ቋሚ ተጠሪው ዓለምአንተ ገብረሥላሴ የአዋጁን ይዘት ለደርግ አባላት ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ኮረኔሉ ባለርስትና ጭሰኛ የሚባል ነገር በሌለበት ሁኔታ አዋጁ ለሰሜን ኢትዮጵያ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው? አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ለሰሜን እና ለደቡብ ኢትዮጵያ

8 በመሬት ስሪቱ "ደቡብ " የተሰኘው የምዕራብና ምስራቅ ጠቅላይ ግዛቶችን ስለሚጠቀልል አደናጋሪ ክፍል ነው። የሰሜኑና የደቡቡ አዋሳኝ መስመር የሚገኘው ከአጠቃላይ የአገሪቱ ጂኦግራፊያዊ ኢጋማሽ ላይ ሳይሆን ወደ ሰሜን ከፍ ብሎ ነው።

9 "Geographical negligence " የሚያመላክተው ፖሊሲዎች በሚረቀቁበትም ሆነ በሚተገበሩበት ወቅት ከስፍራ ስፍራ የሚለያይ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወዘተ ባህሪያቸውን ያላገናዘበ አሰራርን ነው።.

የተለያዩ አዋጆች አንድ ለሰሜን አንድ ለደቡብ አስፈላጊ አይደለም ወይ? ብዬ ጠይቆ እንደነበር አስታውሷል።

በአንድ በኩል ዓለምአንተ ለኮሎኔል ብርሃኑ "*በሰሜኑም ሆነ በደቡብ የተዘረጋው ሥርዓት የተለያየ አይነት ቢሆንም ያው የፊውዳል ሥርዓት ነው። ስለሆነም አዋጁ ለሰሜኑም ለደቡቡም አስፈላጊ ነው። ለአንድ አገር ሁለት አዋጅ ማወጅ አስፈላጊም ተገቢ አይደለም* ብሎ ጥያቄውን መልሶለት ሳለ በተቃራኒው ደግሞ ዓለምአንተ በመጽሐፉ በሰሜኑ እና በደቡቡ የተለያየ አዋጅ ድንጋጌ ይገባ እንደነበር መግለፁ ነው። "*ሁንች አንድ ወጥ መሆን የለባቸውም*' (ገፅ 105)፡ "*ለሁሉም የኢትዮጵያ ግዛቶች በአንድ-ወጥ አዋጅ ማውጣትም ትክክል አይሆንም*' (ገፅ 122) ብሎ መጥቀሱ ተጨማሪ ማጠናከሪያ ወይንም እርምት የሚያሻ ጉዳይ ነው።

## 6. መሬት አዋጁና የብሔር ፖለቲካ

መሬት አዋጁ ከመታወጁ በፊት በመሬት ባለቤቶች እና በአራሽ ገበሬው መሀል የመደብ ልዩነት ነበር። አዋጁ ከታወጀ በኋላ የመሬት ከበርቴ፣ መሳፍንት፣ መኳንንት እና ባላባት የሚባሉ የሶሻል ክላስ ሙሉ በሙሉ ጠፍተዋል። ሆኖም የመደብ ልዩነቱ ከብሔር ወይም ከኃይማኖት ልዩነት ጋር ሲገጥም ደግሞ በመደብ መሀል ያለው ውጥረት የብሔር/ሀይማኖት ስንጥቃትን (*ethno– religious fault lines*) አስከትሎ ሥር ወደ ሰደደ ልዩነት እና ግጭት ይቀየራል። እዚህ ላይ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ በተማሪው እንቅስቃሴ የብሔረሰብ ጥያቄ የፈጠረውን የፖለቲካ ድባብ ልብ ይሏል።

በመሬት አዋጁ ጥያቄ ላይ ትኩረቱ በአመዛኙ በደቡቡ የኢትዮጵያ ክፍል ላይ ሆኖ ከመደብ ልዩነቱ በተደራቢነት የብሔር ጥያቄ ደብዘዝ ብሎ ይንጸባረቅ የነበር ቢሆንም በዓለምአንተ መጽሐፍም ሆነ በደርጉ አባላት ትኩረት አልተደረገበትም። ደሳለኝ (2024) በየካቲቱ አብዮት ወቅት የነበረውን ሁኔታ ሲገልጽ ፖለቲካም ሆነ ኢኮኖሚ ብሔረሰብን ማዕከል አድርጎ የሚሽከረከር ባለመሆኑ፣ ደርግም ይህንን አልተገነዘበውም፣ ይሁን እንጂ የብሔረሰብ ጭቆና የነበረበት ዋነኛው የመሬት ስሪቱ ነው ብሏል።

ኦታዋይ (1977) በሰሜን ኢትዮጵያ ሁለት መደቦች ሲኖሩ አንዳቸውም የመሬት ባለቤት አይደሉም፤አንደኛው ከፋይ ሲሆን ሌላኛው ተቀባይ ሆኖበመሀላቸው የጋራ ሀይማኖት፣ ዘር፣ አብሯቸው የኖረ ባህል እንዲሁም ዝምድናም ጭምር ስላለ በሁለቱ መደቦች መሀል ያለው ልዩነት ጎልቶ አይታይም ይላል። በመሬት ላራሹ አዋጅ ሳቢያ በብዙ የሰሜን አካባቢዎች ተቃውሞ ሲቀሰቀስና ብዙ አካባቢዎች ከመንግሥት ቁጥጥር ሥር ነጻ ሲያደርጉ እንኳ ተቃውሞው ብሔርን ሳይሆን በማኅበራዊ ላይ የተመሠረተ ፀረ-አብዮት ትግል ነበር። እንደ ደቡቡ ክፍል ጎልቶ አይታይ እንጂ በጎጃም ደጋ ዳሞት በመሬት ላዋጁ ማግስት በርካታ ሙስሊም እምነት ተከታይ አርሶ አደሮች ከቀያቸው ተባረው የነበረ ሲሆን መንግሥት ነው በመተከል አውራጃ ቻግኒ አካባቢ ያሰፈራቸው (ገፅ 113)። በሌላ በኩል የደቡብ ጭሰኛው ሀይማኖትና ቋንቋ ከባላባቱ የተራራቀ ነበር። ውድ (1983)

እንደሚያብራራው ባላባቱ ክርስትያኖች ሲሆኑ ጭሰኞቹ እስላሞች ወይንም ሀይማኖት የለሾች ነበሩ፤ በቋንቋ/ብሔርም ልዩነቶች ስለነበሩ በደቡብ የነበረው ቅራኔው ከመደብ ልዩነት ላይ ተነባብሮ የቋንቋ እና የሃይማኖታዊ ገፅታ የታከለበት ነበር። ለምሳሌ በደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ የሰሜን ተወላጆች በቡና እርሻዎች የገበሬ ማህበራት እንዲሳተፉ አለመፈቀዱ እና ጥቃትም ስለተሰነዘረባቸው ቀድሞ የተለመደው ወቅታዊ የሰራተኛ ፍልሰት እንዲቋረጥ በማድረጉ አዋጁ "*ብሔርተኝነት የተላበሰ የመሬት አዋጅ*" ይመስል ነበር (ውድ, 1983)።

የደርጉ የመጨረሻው ጠቅላይ ሚኒስትር ተስፋዬ ዲንቃ (2017) የመሬት አዋጁን በተመለከተ በሰሜኑ እና በደቡቡ ገበሬ መሀል የነበረውን "የውዳሴ ልዩነት" *(enthusiasm gap)* ገልጸዋል። የደቡቡ ገበሬ እጁን ዘርግቶ ደርግን በሙሉ ልብ ከዕቅፉ ሲያስገባውና የገበሬ ማኅበራትን ሲያቋቁም ከሰሜኑ ክፍል ይልቅ በከፍተኛ በፍጥነት ነበር። ይህ ልዩነት የተንጸባረቀው በኢኮኖሚያዊ ጥቅም ልዩነት ሳቢያ ብቻ ሳይሆን ጥንሥሥ የብሔርተኝነት ስሜቶችም ተቀላቅለውበት ያፋጠኑት ሂደት እንደነበር መጠርጠር ይቻላል።

ከላይ ከተጠቀሱት አመላካች ጉዳያት ባሻገር በመሬት ይዞታ መስሪያ ቤቱ የነበረውን የመሬት አዋጁ ተሳታፊዎች አካሄድ በማገናዘብ አንዳቸው ከሌላ ሊገጣጠሙ የሚችሉ በርካታ ነጥቦች በግልፅ ይታዩ ነበሩ። እርግጥ ነው አዋጁ ከመታወጁ ቀደም ብሎ በርካታዎቹ የመስሪያቤቱ ባልደረቦች በተራማጅነት የሚፈረጁና የጋራ ፍላጎታቸው የባላባቱን የጭቆና ቀንበር ለመስበር ነበር። ሆኖም ከአዋጁ መርቀቅ ማግስት ጀምሮ ግን የብሔር ቀመስ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀምረው ነበር። ለምሳሌ በአቶ ዘገየ አማካይነት የተቀጠሩት ሰዎች የብሔረተኛ ስሜት የነበራቸውና ብሔራዊ ሀብት ልማት ያስተዳድራቸው የነበሩ እርሻዎች ለአካባቢው ሕዝብ እንዲሰጡ ፍላጎት እንደነበራቸው (ገፅ 119)፤ የተለያዩ ለውጥ ፈላጊዎችና ተራማጆች መሥሪያ ቤቱን በመቀላቀል የለውጥ አጀንዳቸውን ለማስፈጸም ምቹ መድረክ ሆኖ እንዳገኙት (ገፅ 126)፣ የተወሰኑት የመስሪያ ቤቱ ኤክስፐርቶች ብሔርተኞች እንደነበሩና በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍል ላይ ትኩረት እንደነበራቸው ተገልጿል። በአጭሩ የመሬት ይዞታ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የግራ ፖለቲከኞች "*መካ መዲና*" ወይንም "*የኖህ መርከብ*" እንደነበርና በርካታ ፖለቲከኞች ላቀዱት ግብ መዳረሻነት ሊጠቀሙበት እንደሻቱ መገንዘብ ይቻላል።

ደራሲው ዘግይቶ የተረዳው ጉዳይ ቢሆንም የተለያየ ብሔር-ተኮርና አገራዊ የህቡዕ ርዕዮተ ዓለምን የሚያቀነቅኑ ባለሞያዎች የተከማቹበት፣ ሌሎች አዳዲስ ተቀጣሪዎች የፖለቲካ ማንነታቸውን እያስመሰከሩ የሚቀጠሩበት፣ ሌላው ቀርቶ ተቀጣሪ ያልሆኑ የፖለቲካ አባላትም አዘውትረው የሚጎበኙት መሥሪያ ቤት ነበር። የደራሲው ባልደረባ ሰለሞን ዋዳ በወላይታ የመሬት አዋጁን ተገን አድርጎ "*አካሄደ*" የተባለውን የዘር ልዩነትን መሠረት ያደረገ ቅስቅሳና ሁከት (ገፅ 109) ከብሔር ጉዳይ ጋር ቁርኝት እንዳለው ያሳያል።

ባጭሩ ላለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ የሰፈነው የብሔር ተኮር ፖለቲካ መጀመሪያ በ1962 ዓ.ም በዋለልኝ ፈንድቶ፣ በተማሪው እንቅስቃሴና የፓርቲዎች

መተዳደሪያ ደንቦች ተስተናገዶ፣ ከዚያ በጉዳዩ ላይ የአቋም ክለሳ ተደርጎና ደብዝዞ ቆይቶ (ባሕሩ, 2021 እኤአ)፣ በመሬት ላራሹ አዋጅ ሂደትና ማግስት ዳግም ነፍስ ዘርቶ፣ በ1983 ዓ.ም በህወሓት/ኢሕአዴግ በሽግግር የመንግሥቱ ቻርተር ሆኖ፣ በመጨረሻም በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አማካይነት በኢትዮጵያ ሕጋዊ መሠረት አገኘ? የሚል ጥያቄ ተከታታይ የሚያስነሳ በመሆኑ በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችን ጥናትና ውይይት ይጋብዛል።

## 7. የከሰሙ መልካም ረቂቅ ሃሳቦች

በረቂቅ ውይይቱ ተነስተው የነበሩ ሆኖም በአዋጁ ያልፀደቁ ድንቅ ሃሳቦች ነበሩ። ለምሳሌ አቶ በለጠ በድጋሚ ሚኒስትር ሆነው በደርጉ ከተሾሙ በኋላ የባለስርት ይዞታ ከአንድ ጋሻ እንዳይበልጥ የሚል ሃሳብ (ገፅ 83) አቅርበው ነበረ። ሌላው የእርሻ ሚኒስትር እና ተመራማሪ የነበሩት ዶ/ር ዳኛቸው ይርጉ የአንድ አራሽ ይዞታ ከ10 ሄክታር መብለጥ የለበትም የሚለውን አንቀፅ ተቃውመው (ገፅ 92) ነበር[10]። ዶ/ር ዳኛቸው መሬት ማከራየት የሚከለክለውን አንቀፅም ተቃውመዋል። እኒህ ሃሳቦች ተቀባይነት አግኝተው ቢሆን ኖሮ ገበሬውን በማያፈናቅል ሁኔታ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ በ10 ሄክታር ብቻ ባልተገደበ የግል እርሻዎች ተተግብረውና የትርፍ አዋጭነታቸውን *(Economy of Scale)* ተጠቅመው የግብርናውን በማዘመን ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ባሳደጉት ነበር፤ የደካማ ገበሬዎችን ምግብ ዋስትናም ሊያግዝ በቻለ ነበር።

## 8. መደምደሚያ

ጠቀሜታም ይሁን እኩይ ዓላማ ያላቸው አዋጆች ቢኖሩም ሁሉም እኩል ተጽዕኖ የላቸውም። እኤአ በ1863 በአሜሪካ የባርያ ንግድን የሚያስቆመው አዋጅ እና በእኤአ 1948 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታወጀው ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብቶች ቃል ኪዳን *(Universal Declaration of Human Rights)* በአሜሪካም ሆነ በመላው ዓለም ጎልተው የሚታዩ አዋጆች ናቸው። በኢትዮጵያም በዜጎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅራዊ ህይወት ላይ ዘርፈ-ብዙ የሆነ ተጽዕኖን ካሳረፉ አዋጆች አንዱ በ1987 ዓ.ም በአቶ ክፍሌ ወዳጆ ተዋናይነት ተረቆ የፀደቀውና አሁን በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ነው። ከዚያ ቀደም ብሎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ከተማ ይፍሩ በ1955 ዓ.ም በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ አዋጅ ላይ የተጫወቱትን ቁልፍ ሚና የሚታወስ ነው። ሌላው የዘመናችንን ታሪክ በመሠረታዊነት ተፅዕኖ ካሳደሩ አንኳር አዋጆች መሀል በ"ትውስታዎቼ" የተዳሰሰው የመሬት አዋጁ በመሆኑና መጽሐፉ የተሰናዳው ከአዋጁ አርክቴክቶች መሃል በአንዱ በመሆኑ ለኢትዮጵያ ፋይዳው ከፍተኛ ነው።

በትውስታዎቼ መገንዘብ የሚቻለው ዓለምአንተ፣ ዘገየ አስፋው፣ እና ሌሎች ባልደረቦች በዩኒቨርሲቲ ከተማሩት፣ ከገበሬው ሕይወት ከተገነዘቡት፣ ከኮሚኒስት አገራት የመሬት

10 ዶ/ር ዳኛቸው በመሬት አዋጁ አንዳንድ አንቀጾች ላይ ተቃውሞ በማቅረባቸው በደርጉ ህይወታቸው ተቀጥፏል (ገፅ 97)።

አዋጆች ከቀሰሙት ልምድ እና መረጃዎች፣ ወዘተ ላይ ተመርኩዘው አዋጁን አርቅቀዋል። ወገኝተኝነታቸው በአስከፊ ድህነትና ጭቆና ሲማቅቅ ለነበረው ገበሬ ሲሆን ዓላማቸው ደግሞ የሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ማኅበራዊ ትሩፋትን ለማስገኘት ነበር። ከደርግም ሆነ ከሌሎች ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ይደረግባቸው የነበረውን የፍላጎት ጫና አቻችለው ያረቀቁት አዋጅ ቅንነታቸውን፣ ሐቀኝነታቸውን፣ ቁርጠኝነታቸውን፣ እና ተራማጅነታቸውን የሚመሰክር ታሪካዊ አሻራቸው ነው። ሆኖም ከዓመታት በኋላ ውጤቱ ሲታይ በርካታ ግድፈቶች እንደሚኖሩት እሙን ነው። አርተር ኮናን ዶይል It is easy to be wise after the event (*ኋላ ላይ ጥበበኛ መሆን ቀላል ነው*) እንዳለው ውሎ አድሮ በተገኘ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የትላንቱን የመሬት አዋጅ እሳቤ ጠቅሎ ማጣጣል አግባብ አይሆንም። መስፍን ወልደማርያም (2012) የመሬት አዋጁን ያላዋቂው ደርግ በቅጥ አልባነት ያወጀው ብለው በጥቅል መግለጻቸውም አግባብ አይሆንም። ዓለምአንተም በዚህ መጽሐፍ ያደረገው አብይ ነገር አንዳንድ የአዋጁን መንፈሶችና እሳቤዎች አጽንዖት ሰጥቶ ለማብራራትና ለመከላከል ሞክሯል። ይህ ማለት ግን በአዋጁ ዝግጅት ወቅት የታሰበውና ተከወነው ሁሉ እንከን አልባ ነበረ ማለትም አይደለም።

የመሬት ላራሹ አዋጅ በመላው ኢትዮጵያ ሰፍኖ የቆየውን የባላባቱን ሥርዓት ላንዴ እና ለመጨረሻ አንኮታኩቷል፤ ሊወደስም ይገባል። ሆኖም አዋጁ እንደ አካባቢው ጂኦግራፊያዊ ጠባይ ተቃኝቶ አለመታወጁ በዚህ ዳሰሳ ላይ የተነሳ አንኳር ሂስ ነው። ስለሆነም ከመሬት አዋጁ በኋላ በሰሜኑ እና በደቡቡ ገበሬ የተስተዋሉት የቅበላ ልዩነቶች በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በሥነ ምህዳርም ሆነ በዴሞግራፊው አውድ ላይ የተበላለጠ ጥላ በማጥላቱ በጂኦግራፊያዊም ሆነ ሌሎች የጥናት ሥልቶች ጠልቆ ቢጠና ጠቀሜታው ሰፊ ነው።

## ዋቢ ምንጮች


አበራ የማነ አብ = Yemane-ab, A. (2016). "Land to the tiller": Unrealized agenda of the revolution. *Northeast African Studies*, *16*(1)፡ 39-64.

ባሕሩ ዘውዴ (1999)። የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ። አዲስ አበባ።

ባሕሩ ዘውዴ (2021 እኤአ)። የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ አሻራ በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ። https://www.ethiopianreporter.com/73192/ March 14, 2021።

ቤሉቺ = Bellucci, S. (2016). The 1974 Ethiopian Revolution at 40: Social, Economic, and Political Legacies. *Northeast African Studies*, *16*(1)፡ 1-14.

ብርሃኑ ባይህ (2013)። ያልታሰበው የሕይወቴ ፈታኝ ጉዞ እና የኢትዮጵያ አብዮት ተሳትፎዬ። የኢትዮጵያ አካዳሚ ፕሬስ። አዲስ አበባ።

ኮኸን = Cohen, J. M. (1987). *Integrated rural development: the Ethiopian experience and the debate*. Nordic Africa Institute.

ደሳለኝ ራህሞቶ (2024 እኤአ)። ቢቢሲ አማርኛ ። መሬት ላራሹ፡ የገጠሪቱን ኢትዮጵያ መልክ የቀየረው የተማሪዎች ንቅናቄ። (የካቲት 19, 2024)።
ደሳለኝ ራህሞቶ= Dessalegn Rahmato (2011). Land to Investors: Large-Scale Land Transfers in Ethiopia, Forum for Social Studies, Addis Ababa.
ጋዲስ = Gaddis, J. L. (2005). Strategies of Containment: A Critical Appraisal of American National Security Policy during the Cold War. Oxford University Press.
መስፍን ወልደማርያም (2012)። መሬት፣ መሬት፣ አንድ። ኢትዮ አንድነት ድረገፅ። https://ethioandinet.wordpress.com/2012/01/09/
ነጋ እና ሌሎች = Nega, B., Adenew, B., & Sellasie, S. G. (2003). Current land policy issues in Ethiopia. Ethiopian Economic Policy Research Institute, Addis Ababa, Ethiopia.
ኦታዋይ = Ottaway, M. (1977). Land reform in Ethiopia, 1974-1977. *African Studies Review*, *20*(3)፡ 79-90.
ተስፋዬ ዲንቃ = Tesfaye Dinka (2017)። ETHIOPIA: The Derg Years: An Inside Account. Tsehay Publishers.
ውድ = Wood, A. P. (1983). The decline of seasonal labor migration to the coffee forests of South-West Ethiopia. *Geography*, *68*(1)፡ 53-56.

*ዳንኤል ካሳሁን ዋቅቶላ (ፒኤችዲ)፣ የጂኦግራፊ ተባባሪ ፕሮፌሰር*
*አስተን፣ ቴክሳስ*